# ሃይ ባይ ዘመድ ያጣ አክሎግ ቢራራ

መቸም በክርስቶስ አምሳል የተፈጠረ የሰው ልጅ ሆኖ በኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችን ላይ የተፈጸመውን ዘግናኝና ፍጹም አረመንያዊ ተግባር ሰምቶና አይቶ ልቡ ያልደማ ወገን አለ ብየ አላስብም። ይህ ወደር የማይገኝለት የሽብርተኞች የጭካኔ ተግባር ለትውልድ የማይረሳ ጠባሳ ሆኖ ይኖራል። ለዚህም ነው ዘግናኝ ወሬው እንደተሰማ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከጫፍ እስከ ጫፍ ባገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሐዘኑና ቁጭቱን ባንድ ድምጽ የገለጸውና እየገለጸ ያለው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን በወገን ስቃይና ሰቆቃ ለመጠቀምና ለመነገድ ሁሌ አኮብኩበው የሚጠብቁ ግለሰቦች ይሄውና ከየተወሸቁበት ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል። ይህ ክስተት አንዱ አንዱን የሚከስበት ሳይሆን ሁሉም ባንድ ድምጽ አረመንያዊ ተግባሩን የሚኮንንበት ከዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ ጋር በመሆን ሽብር የሚገታበት መንገድ የሚያጤንበት ወቅት ነው።ለዚህ አልታደልንምና ይሄውና ልክ እንደአሸባሪዎቹ ሐይማኖት ሽፋን አድርገው እንደሚንቀሳቀሱት የአሸባሪዎችን ተግባር እንደ ሽፋን በመጠቀም ለከንቱና ርካሽ ዓላማቸው ማስፈጸሚያ ለማድረግ ሲኳትኑ ይስተዋላሉ። እነዚህ የሰው አተላዎች በነዚህ ሰማእታት ደም ለመነገድ ሲውተረተሩ የለመደባቸው ስለሆነ ትንሽ እንኳን አይሰቀጥጣቸውም።

ከነዚህ የሰው አረም አንዱ አክሎግ ቢራራ( ዶር) ነው። ይህ ግለ ሰብ በኣለም ባንክ ይሰራ እንደነበር ሁሉም የሚያውቀው ነው። ከስራው ጡረታ ከወጣ በሁዋላ ግን የኢትዮጵያ ፖለቲካ እንደመደበሪያ አድርጎት በየጊዜው ሲሞነጫጭር ይስተዋላል። መቸም የዘመኑ ቴክኖሎጂ የፈጠረው ነውና ማንም እየተነሳ የፈለገውን ቢጽፍና በየዌብ ሳይቱ ቢለጠፍ ቁምነገር ያለውን በቁምነገርነቱ አሉባልታው ደግሞ ለመደበሪያ እንደሁኔታው እናነበዋለን።

የአሁኑ ክስተት ግን ልዩ ስሜት የፈጠረብን ልባችን በሐዘን የተሰበረበት ክስተት ነው። በዚህ ዙርያ የሚጻፉ ሁሉ በብስለተና ጥንቃቄ የታከለበት መሆን ይገባዋል። ከጨቅላ አስተሳሰብ ተነስተህ ሌላው ሕዝብ ባንተ ደረጃ አውርደህ ለማናጋትና ለማበጣበጥ መነሳት ግን ከንቱነት ነው።

አክሎግ ቢራራ ካሁን በፊት ብዙ የቀባጠረ ቢሆንም በብዙ ሰው ለትዝብት የጣለውና ከንቱነቱና ባዶነቱን በግላጭ ያስመሰከረበት የህዳሴው ግድብ በተመለከተ ነው። ለዚህ ደግሞ ሙሁራዊ ሂስና አስተያየት በፕሮፌሰር ተኮላ ሐጎስ መልስ ተሰጥቶታል። ለኔ ግን ባዶነቱና ከንቱነቱን በበለጠ እንዳረጋግጥ አድርጎኛል። በጣም ስሜቴ የጎዳው ግን “ ከጩኸት ወደ ተግባር” በሚል ርእስ በሊቢያ በረሃ በወንድሞቻችን ስለተፈጸመው ግፍ  አስመልክቶ የጻፈውን ነው። በሱ የእውቀት አድመስ የኢትዩጵያን ሕዝብ ማተራመስ የሚቻለው ጊዜው አሁን ነው ከሚል በጣም ግብዝ ከሆነ አስተሳሰብ ተነስቶ ነው። እዚህ ላይ በርግጠኝነት ለመናገር የምችለው አክሎግ ቢራራ የኢትዮጵያን ሕዝብ በትክክል እንደማያውቅ ነው። ምክንያቱም አክሎግ ከኢትዮጵያ የወጣበት በትክክል ባላውቀውም ከ 35 ዓመት በላይ እንዳሰቆጠረ የሚያውቁት ይናገራሉ። ከዚህ በመነሳት አክሎግ ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ሲጽፍና ሲተነትን ከ35 ዓመት በፊት ስለሚያውቃት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ነው። የቆመ ሰዓት ይሉሃል እንዲህ ዓይነት ነው።  የኢትዮጵያ ህዝብ መቃወም ሲፈልግ ምክንያት አይጠብቅም።ሰበብ ፈልጎ ያዙኝ ልቀቁኝ

አይልም። እንዲያ ቢሆን ኑሮማ ብዙ አጋጣሚዎች አልፈዋል። በንዲህ ያለ ሁኔታ ውስጣዊ ቅሬታውን ወደ ሁለተኛ ደረጃ አውርዶ አንድነቱን በበለጠ አጠናክሮ ውጫዊ ጠላቶቹን የመመከት ታሪክና ባህል ያለው ህዝብ ነው።
ባንድ ወቀት ከአክሎግ ቢራራ በወቅታዊ የኢትዮጵያ ጉዳይ ሲከራከሩ የነበሩ ሰው ያሉኝን አስታወሰኝ፡ እሳቸው የሚያውቁት ክስተት አንስተው ሲከራከሩ አክሎግ ከጭፍን ጥላቻው ተነስቶ የተፈጠረው ክስተት በመንግስት ሊያላክክ ሲፈልግ ሰውየው ጉዳዩ ይከታተሉት ስለነበር መንግስት እዚህ ላይ ምንም እጅ እንደሌለው ሊያስረዱት ቢሞክሩ ሃቁን ሊቀበላቸው አልፈለገም፤ በዚህ የተበሳጩት ሰው አክሎግ የት ነበር የሚሰራው ብለው ጠየቁ፤ ዓለም ባንክ ነበር የሚሰራው ተብሎ ሲመልስላቸው " አክሎግን ሳይሆን ዓለም ባንክን ናቅኩት" አሉ።
በመጨረሻ ልለው የምፈልግ አንድ ሰው ስለ አገር ሲያስብ  መጀመሪያ ስለ ቤተሰቡ ቀጥሎ ስለጎረቤቱ እያለ መሆን አለበት። አክሎግ ቢራራ ስለቤተሰቡ፤ ጎረቤቱ ያለው ታሪክ ምን ይመስላል። ይህች ጥያቄ ዶክተር አክሎግን የምትመለከት ሆና በሰከነ አእምሮ አስቦ ንሰሐ የሚገባበት ወቀት አሁን መሆኑ ላስገነዝበው እፈልጋለሁ።

ምንም እንኳን ሐዘኑ የሁላችን ቢሆንም፤ በግፍ ለተጎዱት ቤተሰብ መጽናናቱን እመኛለሁ።
ኢትዮጵያ ለዘልአለም በልጆችዋ ተከብራ ትኖራለች!

ውለታው ከሲያትል